የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፩
አዲስ አበባ ጥቅምት ፲፰ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

18[th] Year No. 1
ADDIS ABABA 28[th] October 2011

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፶፮/፪ሺ፬

የኢትዮጵያ ካይዘን ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ገጽ ፮ሺ፩፻፺፰

**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፶፮/፪ሺ፬**

**የኢትዮጵያ ካይዘን ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፭ እና አንቀጽ ፴፬ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ካይዘን ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፶፮/፪ሺ፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

፩/ "ካይዘን" ማለት የማያቋርጥ የጥራትና ምርታማነት ማሻሻያ አስተሳሰብና መሳሪያ ነው፤

፪/ "ሚኒስቴር" ማለት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነው፤

፫/ "የካይዘን አማካሪ" ማለት የማምረቻና አገልግሎት ተቋማትን ስለካይዘን አስተሳሰብና መሣሪያዎች ለማሰልጠንና ለማማከር ብቁ የሆነ ሰው ነው፤

፬/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል፡፡

| | |
|---|---|
| ያንዱ ዋጋ Unit Price | 3.65 |

## CONTENTS

Regulation No. 256/2011

Ethiopian Kaizen Institute Establishment
Council of Ministers Regulation....... Page 6198

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 256/2011**

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF ETHIOPIAN KAIZEN INSTITUTE**

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 and Article 34 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010.

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as the "Ethiopian Kaizen Institute Establishment Council of Ministers Regulation No. 256/2011".

2. **Definitions**

In this Regulation, unless the context otherwise requires:

1/ "kaizen" means ongoing quality and productivity improvement concept and tools;

2/ "Ministry" means the Ministry of Industry;

3/ "kaizen consultant" means a qualified person to train and consult the manufacturing and service rendering organizations in the kaizen concept and tools;

4/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

| | |
|---|---|
| P.O. Box ፖ.ሣ.ቁ | 80,000 |

## ፫. መቋቋም

፩/ የኢትዮጵያ ካይዘን ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ "ኢንስቲትዩት" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

፪/ ኢንስቲትዩቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

## ፬. ዋና መሥሪያ ቤት

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል።

## ፭. የኢንስቲትዩቱ ዓላማ

የኢንስቲትዩቱ ዓላማ መሰረተ ሰፊና የማያቋርጥ የጥራትና ምርታማነት ማሻሻያ ሥራዎችን በማከናወን ተወዳዳሪ ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋት ይሆናል።

## ፮. የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባራት

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩/ የካይዘን አስተሳሰብና መሳሪያዎችን ለማስረጽ የሚያስችል ስትራቴጂና ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ያስፈጽማል፤

፪/ የመንግስትን ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን ለማስፈጸም የሚያበቃ ሀገራዊ የጥራትና የምርታማነት ንቅናቄ ለመፍጠር የሚያስችሉ ሥራዎችን ያከናውናል፤

፫/ ለጥቃቅን፣ ለአነስተኛ፣ ለመካከለኛ እና ለከፍተኛ የማምረቻ ተቋማት የካይዘን ማስተማሪያና የምክር አገልግሎት መስጫ ማንዋሎችን ያዘጋጃል፣ ያሰራጫል፣ አፈጻጸማቸውንም ይከታተላል፤

፬/ ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ለሚሰጡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ባለሙያዎች የካይዘን ሥልጠናና የማማከር አገልግሎት የአሰልጣኞች ሥልጠና ይሰጣል፣ አፈፃፀሙንም ይደግፋል፣ ይከታተላል፤

፭/ ለመካከለኛና ከፍተኛ ተቋማት የካይዘን ሥልጠናና የማማከር አገልግሎት ይሰጣል፤

፮/ በአገልግሎት ሰጪና በትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የካይዘን አስተሳሰብንና መሳሪያዎችን በየደረጃው ለማስረጽ የሚያስችሉ የሥልጠና፣ የማማከርና የማስተባበር ሥራዎችን ያከናውናል፤

## 3. Establishment

1/ The Ethiopian Kaizen Institute (hereinafter the "Institute") is hereby established as an autonomous federal government office having its own legal personality.

2/ The Institute shall be accountable to the Ministry.

## 4. Head Office

The Institute shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

## 5. Objective of the Institute

The Institute shall have the objective to carry out broad based activities of ongoing quality and productivity improvement and thereby enhance the expansion of competitive industries.

## 6. Powers and Duties of the Institute

The Institute shall have the powers and duties to:

1/ formulate strategy and plan that assist in the dissemination of the kaizen concept and tools, and implement same upon approval;

2/ create country wide quality and productivity movement that could enable to effectively implement government policies and strategies;

3/ prepare and distribute kaizen training and consultancy manuals customized to micro, small, medium and large enterprises, and follow up their applications;

4/ provide training of trainers to technical and vocational education and training institutions' industrial extension experts so as to enable them to be capable to provide kaizen training and consultancy to micro and small enterprises, support and follow up the implementation of same;

5/ provide kaizen training and consultancy service to medium and large companies;

6/ undertake training, consulting and coordinating activities to disseminate kaizen concepts and tools at all levels of service providers as well as educational and training institutions;

**፫. መቋቋም**

፩/ የኢትዮጵያ ካይዘን ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ "ኢንስቲትዩት" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

፪/ ኢንስቲትዩቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

**፬. ዋና መሥሪያ ቤት**

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል።

**፭. የኢንስቲትዩቱ ዓላማ**

የኢንስቲትዩቱ ዓላማ መሰረተ ሰፊና የማያቋርጥ የጥራትና ምርታማነት ማሻሻያ ሥራዎችን በማከና ወን ተወዳዳሪ ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋት ይሆናል።

**፮. የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባራት**

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

፩/ የካይዘን አስተሳሰብና መሳሪያዎችን ለማስረጽ የሚያስችል ስትራቴጂና ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀ ድም ያስፈጽማል፤

፪/ የመንግስትን ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን ለማ- ስፈጸም የሚያበቃ ሀገራዊ የጥራትና የምርታ- ማነት ንቅናቄ ለመፍጠር የሚያስችሉ ሥራዎ- ችን ያከናውናል፤

፫/ ለጥቃቅን፣ ለአነስተኛ፣ ለመካከለኛ እና ለከፍተኛ የማምረቻ ተቋማት የካይዘን ማስተማሪያና የምክር አገልግሎት መስጫ ማንዋሎችን ያዘ ጋጃል፣ ያሰራጫል፣ አፈጻጸማቸውንም ይከታ ተላል፤

፬/ ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ለሚሰጡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ባለሙያዎች የካይዘን ሥልጠናና የማማከር አገልግሎት የአሰልጣኞች ሥልጠና ይሰጣል፣ አፈፃፀሙንም ይደግፋል፣ ይከታተላል፤

፭/ ለመካከለኛና ከፍተኛ ተቋማት የካይዘን ሥልጠናና የማማከር አገልግሎት ይሰጣል፤

፮/ በአገልግሎት ሰጪና በትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የካይዘን አስተሳሰብንና መሳሪያዎችን በየደረጃው ለማስረጽ የሚያስችሉ የሥልጠና፣ የማማከርና የማስተባበር ሥራዎችን ያከናውናል፤

**3. Establishment**

1/ The Ethiopian Kaizen Institute (hereinafter the "Institute") is hereby established as an autonomous federal government office having its own legal personality.

2/ The Institute shall be accountable to the Ministry.

**4. Head Office**

The Institute shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

**5. Objective of the Institute**

The Institute shall have the objective to carry out broad based activities of ongoing quality and productivity improvement and thereby enhance the expansion of competitive industries.

**6. Powers and Duties of the Institute**

The Institute shall have the powers and duties to:

1/ formulate strategy and plan that assist in the dissemination of the kaizen concept and tools, and implement same upon approval;

2/ create country wide quality and productivity movement that could enable to effectively implement government policies and strategies;

3/ prepare and distribute kaizen training and consultancy manuals customized to micro, small, medium and large enterprises, and follow up their applications;

4/ provide training of trainers to technical and vocational education and training institutions' industrial extension experts so as to enable them to be capable to provide kaizen training and consultancy to micro and small enterprises, support and follow up the implementation of same;

5/ provide kaizen training and consultancy service to medium and large companies;

6/ undertake training, consulting and coordinating activities to disseminate kaizen concepts and tools at all levels of service providers as well as educational and training institutions;

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ የተመለከቱትን የኢንስቲትዩትን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የኢንስቲትዩቱን ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት እንዲሁም የኢንስቲትዩቱን ዓላማ በማስፈጸም ሥራ ላይ የሚሠማሩ ባለሙያዎችን የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የኢንስቲትዩቱን ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ አመታዊ ዕቅድ፣ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ) ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

ረ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል::

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኢንስቲትዩቱ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል::

**፲፪. በጀት**

የኢንስቲትዩቱ በጀት በመንግሥት ይመደባል::

**፲፫. የሂሳብ መዛግብት**

፩/ ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል::

፪/ የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ::

**፲፬. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ ጥቅምት ፲፯ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

a) exercise the powers and duties of the Institute specified under Article 6 of this Regulation;

b) employ and administer employees engaged in support services of the Institute in accordance with the federal civil service laws and, in the case of employees engaged in the core functions of the Institute, in accordance with directives approved by the government following the basic principles of the federal civil service laws;

c) prepare and submit to the Ministry the strategic plan, annual plan, work programs and budget of the Institute and implement same upon approval;

d) effect payments in accordance with the approved budget and work program of the Institute;

e) represent the Institute in its dealings with third parties;

f) prepare and submit to the Ministry the performance and financial reports of the Institute.

3/ The Director General may delegate part of his powers and duties to other officers and employees of the Institute to the extent necessary for the effective performance of the activities of the Institute.

**12. Budget of the Institute**

The budget of the Institute shall be allocated by the government.

**13. Books of Accounts**

1/ The Institute shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts and financial documents of the Institute shall be audited annually by the Auditor General or an auditor assigned by him.

**14. Effective Date**

This Regulation shall come into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 28th day of October, 2011.

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

፯/ ተቋማት ካይዘንን እንዲተገብሩ እና የጥራትና የምርታማነት ባህልን እንዲያዳብሩ የሚያነቃቃ የአሰራር ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፣ አተገባበሩንም ይከታተላል፤

፰/ የካይዘን የጥራትና ቁጥጥር እና የምርታማነት ማሻሻያ ቡድኖች በየተቋማቱ እንዲመሠረቱ የድጋፍ ሥራዎችን ያከናውናል፣ የተገኙ ውጤቶችን ይመዘግባል፣ ዕውቅናም ይሠጣል፤

፱/ በካይዘን ሥልጠናና የማማከር አገልግሎት ተጠቃሚ ለሆኑ የላቀ አፈፃፀም ለሚያሳዩ ድርጅቶች የዕውቅናና ማበረታቻ ሥርዓት ያዘጋጃል፣ ያስፈጽማል፣ የጥራት ምልክትም እንዲያውለበልቡ ይፈቅዳል፤

፲/ በካይዘን የተገኘውን መሻሻል ለመለካት የሚያስችሉ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ ያሳትማል፣ ያሰራጫል፤

፲፩/ የካይዘን ትግበራን አፈፃፀም ለመገምገም የሚያስችሉ የውጤት መለኪያዎችን ያዘጋጃል፣ በተግባር ላይም ያውላል፤

፲፪/ ለካይዘን አሰልጣኞችና አማካሪዎች የብቃት ግምገማና ማረጋገጫ ሥርዓት ይዘረጋል፤

፲፫/ የካይዘን ትግበራ ምርጥ ተሞክሮ የመቀመር፣ የማስፋፋትና ሞዴል ድርጅቶችን የማፍራት ሥራዎችን ያከናውናል፣ ዓመታዊ ሕትመቶችን ያዘጋጃል፣ ያሰራጫል፤

፲፬/ የጥራት ወርን በመሰየም በሃገር አቀፍ ደረጃ የመወያያና የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ያዘጋጃል፤

፲፭/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

፲፮/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

፯. <u>የኢንስቲትዩቱ አቋም</u>

ኢንስቲትዩቱ፡-

፩/ ምክር ቤት፤

7/ cause the establishment and follow up the implementation of, a system that induces organizations to implement kaizen and develop the culture of pursuing quality and productivity;

8/ support organizations to establish quality control circles and continuous productivity improvement circles and register and acknowledge their performances;

9/ prepare and implement a system of recognition and provide incentives to beneficiary organizations in kaizen training and consultancy services that manifest excelled performances; and authorize them to display quality emblem;

10/ collect, compile, publish and disseminate indicators enabling to measure improvements obtained as a result of kaizen;

11/ prepare and implement key performance indicators enabling to evaluate kaizen implementation results;

12/ establish evaluation and qualification systems for kaizen trainers and consultants;

13/ organize and expand best kaizen practices, and produce kaizen model companies; prepare and distribute annual publications;

14/ designate quality month and organize country wide discussion and awareness creation forums;

15/ own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name;

16/ perform such other related activities necessary to the attainment of its objectives.

7. **<u>Organization of the Institute</u>**

The Institute shall have:

1/ a Council;

፪/ በመንግስት የሚሾሙ ዋና ዳይሬክተር እና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣ እና

፫/ አስፈላጊው ሠራተኞች፣

ይኖሩታል፡፡

፰. **የምክር ቤቱ አባላት**

፩/ የምክር ቤቱ አባላት አግባብነት ካላቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ከግሉ ዘርፍ የተውጣጡ ሆነው በመንግስት ይሰየማሉ፡፡

፪/ የምክር ቤቱ አባላት ቁጥር እንደ አስፈላጊነቱ ይወሰናል፡፡

፱. **የምክር ቤቱ ተግባራት**

ምክር ቤቱ፡-

፩/ ጥራትንና ምርታማነትን ለማሻሻል በኢንስቲትዩቱ የሚዘጋጁ የካይዘን ስትራቴጂዎችንና ዕቅዶችን ይመረምራል፣ ያጸድቃል፤

፪/ በኢንስቲትዩቱ የተዘጋጁ የአቅም ግንባታ መርሃ ግብሮችን ይመረምራል፣ ያጸድቃል፤

፫/ የኢንስቲትዩቱን የዕቅድ አፈጻጸም በየሦስት ወሩ ይገመግማል፣ የማስተካከያ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል፡፡

፲. **የምክር ቤቱ ስብሰባዎች**

፩/ ምክር ቤቱ በየሦስት ወሩ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፪/ ከምክር ቤቱ አባላት መካከል አብዛኞቹ በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

፫/ የምክር ቤቱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፲፩. **የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር**

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ የኢንስቲትዩቱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

2/ Director General and, as may be necessary, Deputy Director Generals to be appointed by the government; and

3/ the necessary staff.

8. **Members of the Council**

1/ Members of the Council shall be drawn from the appropriate government offices and the private sector and be appointed by the government.

2/ The number of members of the Council shall be determined as required.

9. **Duties of the Council**

The Council shall:

1/ review and approve kaizen strategies and plans formulated by the Institute with a view to improving quality and productivity;

2/ review and approve capacity building programs developed by the Institute;

3/ evaluate the implementation of plans of the Institute every three month and set direction for improvement.

10. **Meetings of the Council**

1/ The Council shall convene its ordinary meetings every three month; provided, however, that it may hold extraordinary meetings at any time as may be necessary.

2/ There shall be a quorum where the majority of the members of the Council are present at a meeting.

3/ The decisions of the Council shall be passed by majority vote and, in the case of a tie, the Chairperson shall have a casting vote.

4/ Without prejudice to the provisions of this Article, the Council may adopt its own rules of procedure.

11. **Powers and Duties of the Director General**

1/ The Director General shall be the chief executive officer of the Institute and shall direct and administer the activities of the Institute.

2/ Without prejudice to the provision of sub-article (1) of this Article, the Director General shall: